# <u>ምርጫ 2002 ትያትር እና አደገኛነቱ</u>

በመጪው ግንቦት እንደሚካሄድ ብዙ የሚባልለት አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ባለፉት አስርተ አመታት ከተካሄዱት የአፍሪካ አገሮች ምርጫ ፣ ምዝገባ ፣ ድምጽ አሰጣጥ እና የቆጠራ ውጤት አንጻር ሲመዘን የአሸናፊው ማንነት ከወዲሁ የታወቀ ነው ማለት ይቻላል።

ወያኔ ኢህአዴግ ይህን ምርጫ የሚያደርገው በታሪክ አጋጣሚ ስልጣን በተቆናጠጠ ማግስት ወግ አይቅርብኝ ብሎ ለአለም አቀፍ ተቀባይነት ሲል ብቻ ሕገ መንግስት አርቅቆ በህዝብ አጸደቅሁ በማለት እርሱ ባወጣው ህገመንግስት አስገዳጅነት ከላይ እስከታች የራሱን አሻንጉሊቶች በአስመራጭነት ሰይሞ በየአምስት አመቱ ዓለምን ያሞኛል ያታልላል።

በነገራችን ላይ ኢህአዴግ ሰነፍ አይደለም መኖር አለበት ለመኖር በሚቻለው ሁሉ ያለ እንቅልፍ መሰሪ ተንኮሉን በየአምስት አመቱ መቀያየሩ የግድ ይላል። አለያማ ( በምርጫ ካላሸነፈ ) ከነተለጣፊዎቹና ትርፍራፊ ተቋዳሾቹ የሚጠብቀው ሞት እስራት እና ውርደት ከመሆኑም በላይ ከኢትዮጵያ ህግ አልፎ በአለም አቀፍ ደረጃ በሚያስጠይቅ ለብዙ መቶ ሺዎች የነፍስ መጥፋት ወንጀል ተጠያቂነቱን አሳምሮ ያውቃልና።

በመሆኑም ጊዜ የሰጠውን አመቺ ሁኔታ ማለትም የመራጩን ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ችግር፣የአገሪቱን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ፣ የወቅቱን አለም አቀፋዊ አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ በተሚላ ስልታዊ የማጭበርበር ቲያትር ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለትን ለማሸነፍ እርግጠኛ ሆኖ ተቀምጧል።

ኢህአዴግ ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለትን ለማሸነፍ የተጠቀመባቸው እና እየተጠቀመባቸው ያለ መሰሪ ስልቶች በቅርቡ ከሀገሬ ህይወቴን ለማቆየት አሁን ለምገኝበት መራራ የስደት ህይወት እስከተዳረግሁበት ጊዜ ድረስ የማውቀውን ላስነብባችሁ።

አዎን የወቅቱ አለም አቀፋዊ አሸባሪነት ለኢህአዴግ ተውኔት ዋነኛ አጋጣሚ ሆኖለታል ማለት ይቻላል። እንዴት ብትሉኝ በምስራቅ አፍሪቃና አካባቢዋ ከፍተኛ የአሸባሪዎች መዘዋወሪያ ፣ መሰልጠኛ እና መደራጃ ሆኗል በሚል ከታየውና ከሚታየው በላይ አጋንኖ መረጃ በማቅረብ ለአሜሪካና ለደጋፊዎቿ ቀልብ የሳበ መንግስት ቢኖር ኢህአዴግ በቀዳሚነት የሚገኝ መሆን በመቻሉ ነው። የተጋነነ መረጃ በመስጠትም አላቆመም ፍላጎቴ ከተሟላልኝ በአካባቢው ያለውን የአሸባሪዎች እንቅስቃሴ መከላከል ፣ ማጥቃት እና ጨርሶ በቁጥጥር ስር ማድረግ እችላለሁ! ብሎ ለአሜሪካና እንግሊዝ መንግስታት ቃል በመግባቱ ዘመናዊ የጦር እና ስለላ መሳርያዎችን እንዲሁም የተትረፈረፈ የገንዘብ ስጦታን ተችሯል። ከዚህም በላይ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሃያላኑን መንግስታት ጆሮ ያጡበትን ከፍተኛ ድል ተቀዳጅቷል።

ጉዳዩን በመጠኑ ለማብራራት ምርጫ 97 ውጤቱ ለወያኔ አስደንጋጭ የነበረ ቢሆንም ሽንፈቱን ክዶና አጭበርብሮ በስልጣን የቆየው ኢህአዴግ ከድንጋጤው ሳይረጋጋ ወዲያው በህዝብ አለመመረጡን በውስጥ አሰራሩ አምኖበት ለቀጣዩ ምርጫ የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ ዝግጅቱን ጀመረ።

በውጭ ሃያላን ሀገሮች ተቀባይነት የማግኘቱን ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻውን ባለ አቅሙ ከማጧጧፍ በተጓዳኝ በሃገር ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ያተረፉና ከውጭ መንግስታት ጋርም ግንኙነት ለማድረግ ችሎታውና አቅሙ ያላቸውን የተቃዋሚ ፓርቲ ዋነኛ ታዋቂ ግለሰቦች በእስራት ከፖለቲካው መድረክ ዞር የሚሉበትን ስልት ቀይሶ በሰበብ አስባብ ቃሊቲ እስር ቤት አጎራቸው።

በመላው ሀገሪቱ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይካሄድ በአዲስ አበባ ከ 200 በላይ ሰላማዊ ሰዎችን በጥይት በመደብደብ ለሰው ልጅ ደንታ የሌለው ጨካኝ ባለ ጡንቻነቱን አረጋገጠ።

ከጎረቤት አገር ከሚገኙ አሸባሪዎች ጋር እታገላለሁ የሚል እቅዱን ወደ ተግባር ለመተርጎም ሶማሊያ አደገኛ ጥቃት ልትሰነዝርብን ነው የሚል ሰበብ ፈጥሮ እና የመከላከልን አስፈላጊነት

ከሽኖ ለራሱ አሻንጉሊት ምክር ቤት አቅርቦ በማፀደቅ ፈጥኖ ወደ ጦርነቱ ገባ። በዚህም የኢህአዴግ ድብቅ አላማ ሳቢያ የሺዎች ንፁሃን ዜጎች በውትድርና ተማግደዉ በአሰቃቂ ሁኔታ በኢትዮጵያ ስም ሞቱ።

በሐገር ውስጥ በእስረኝነት ቀለበት ውስጥ ያልገቡትን ተቃዋሚ ፖለቲከኞች በገንዘብ ሀይል በውስጣቸው አንጃ ፈጥሮ እርስ በእርስ በማቆራቆስ አቅጣጫቸውን ማሳት ዋና ስራው አድርጎ ተያያዘው።

በዚህ ሁኔታ ከሓገር ውስጥ አልፎ በውጭ ያለውን የተቃዋሚዎች ጩኸት ሰሚ የማሳጣቱን አቅም አጠናክሮ አሸባሪነትን በመታገል ላይ ያተኮረ ከበርቴ መንግስታት በምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ ለሚከሰት ማናቸውም የአሸባሪዎች እንቅስቃሴ ከአካባቢው ኢትዮጵያን ብቸኛዋ ስትራነጂ አገር ምርጫቸው ካደረጉ በኋላ ሌላ አዲስ መንግስት ተቋቁሞ ከመደራደር በመስመራቸው የገባውን ለማዳ በምስጢራዊ ግንኙነት በላቀ ደረጃ አጠናክሮ ተልእኮውን እንዲወጣ ወያኔ ሲመረጥ የአይዞህ ባይነት ህልሙን በእጁ ጨበጠ። በአንጻሩ ለተቃዋሚዎች ከዲፕሎማሲያዊ ጥርስ ያላለፈ እርዳታ ጨርሶ በማስነፈጉ ለወያኔ ሰርግ ሆነለት።

ቀሪው ትኩረት ለቀጣዩ ምርጫ ድምጽ ማሰባሰቢያና ከእስካሁኑ ለየት ያለው ለአሸናፊነት የሚያበቃውን እቅድ በስራ ላይ ሲያውል፦

- በተለያዩ ኢህአዴግ በተሸነፈባቸው ከተሞች ልዩ የወጣት እና የሴቶች በስራ አጦችና የቤት እመቤቶች ላይ ያተኮረ በየቀበሌው ስውር አደራጅ ግብረ ሃይል አሰማርቶ በማቋቋም ከኢህአዴግ ሃሳብ ጋር ለሚስማሙ ወርሃዊ ጠቀም ያለ ገንዘብ በመክፈል፡

- በዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች ጨርሰው ከመውጣታቸው በፊት የኢህአዴግን ፕሮግራምና ደንብ ተቀብለው አባል ካልሆኑ ስራ የማያገኙ መሆኑ እየተነገራቸው ባያምኑበትም በአባልነት የተመለመሉትን እንደተመረቁ ከወያኔ ህልውና በተያያዙ የስራ ዘርፍ እንዲመደቡና በአይነቁራኛ እየተጠበቁ እንዲሰሩ በማድረግ

- በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ስራ ለመቀጠር ከአነስተኛ የስራ መደብ፦ ጽዳትና ተላላኪ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ሃላፊነት የኢህአዴግ አባል ካልሆነ ስራ እንዳይቀጠር በማድረግ

- የኢህአዴግ አባል ለመሆን የሚያቅማሙና አስፈላጊነታቸውን የሚያምንባቸውን ቋሚ ገቢ የሌላቸውን በግል ወይም በጋራ የንግድ ድርጅት ማቋቋም እንዲችሉ የከተማ ቦታ ንግድ ፈቃድና ድጎማ ገንዘብ በመስጠት

- በህዝብ ስም በታላላቅ ከተሞች ለመኖሪያ የተሰሩ የጋራ ህንጻዎች የኢህአዴግን ቁልፍ ቦታ ለያዙ በመስጠትና በመሸጥ የደጋፊዎቹን ቁጥር ለማሳደግ ከተጠቀመባቸው ስልቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህንን በመሳሰሉ ሌሎች ዘዴዎችም ጭምር በከፍተኛ ትንቅንቅ ተጠናክረው ገዢውን መንግስት በተወዳዳሪነት ለመጣል የሚንቀሳቀሱትን ከማዳከም ጎን ለጎን የበርካቶችን የመኖር ህልውና ከኢህአዴግ ህልውና ጋር አቆላልፎ ባለ ጥሩ አትራፊ የንግድ ድርጅት ባለቤት፡ ያለችሎታ የከፍተኛ ደሞዝና ስልጣን ባለቤት፡ ሳይሰሩ በየወሩ ደሞዝ ተከፋዮችን ቁጥር በእጅጉ አብዝቶ በወያኔ ሳንባ የሚተነፍሱ ኢህአዴግ ከሌለ እስትንፋሳቸው እንደሚቆም አድርገው የሚያስቡ ሲላቸው ኢህአዴግን የሚቃወሙ መስለው የሚቅበዘበዙ የእናት ሃገር ጡት ነካሾች ቁጥር በእጅጉ አበርክቶ ይገኛል።

በተገኘው አጋጣሚ ተወዳዳሪ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማስከፋት ተቆጥተው ስልት የሌለው ጉዞ እንዲጓዙና ከምርጫው ተፈናጥረው እንዲወጡ አልፎተርፎም ያለ አለም አቀፍ ታዛቢ እራሱ ከእራሱ ጋር ተወዳድሮ ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለትን ውጤት ከቀድሞው በላቀ የአጭበርባሪ ተዋኒያን ታጅቦ ያለተወዳዳሪ ድሉን በእጁ እንደሚያደርግ እርግጠኛ ሆኖ ቀኑን ይጠባበቃል።

የመጨረሻውና የአሁኑ የወያኔ መልካም አጋጣሚ የምለው የአንድ አመት እድሜ ያስቆጠረው የአሜሪካው የኦባማ መንግስት አቅጣጫ ከጅምሩ ከሙስና ያልጸዱ እና ዲሞክራሲን በትክክል የማይተገብሩ የአፍሪካ መንግስታት እና መሪዎቻቸው አይስማሙኝም የሚል አቋሙን ገልጾ የነበረ ቢሆንም እምነቱን በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ ተስኖት በሶማሊያ በየመንና በኤርትራ በመታየት ላያ ላለው የአሸባሪዎች ሁኔታ ኢህአዴግን በጥንቃቄ በተቃኘ ጥበብ የማቆየት አስፈላጊነት ገመጋረጃ ጀርባ የአሜሪናውያን ጠረን አይሎ እና ገንኖ ይተነፍጋል::

በዚሁ መጠን ትግሉ እንዲቀጥል ለማድረግ ወሳኝ ነን በሚሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና መሪዎቻቸው በአላማቸው ጸንተው ሲቆዩና የትግል ስልቶቻቸውን በኢህአዴግ መጠን ለአሸናፊነት በሚያበቃ ተርታ ደርጅተው አይታዩም:: አንድነትና ኢትዮጵያዊነት በወሬ ወይም በወረቀት ላይ ብቻ ካልሆነ በስተቀር እስከመጨረሻው አይተገበርም::

ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሰውና እያደረሰ ያለው ኢሰብአዊ ግፍና በደል በብዙሃን ልብ ውስጥ ተዳፍኖና ታምቆ የሚፈነዳበት እጅግ አደገኛ ቀን መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ነው:: መጨው አደገኛ ቀን ደግሞ የሚጎዳው እኛኑ ኢትዮጵያንን ካልሆነ በስተቀር ዛሬ እርስ በርስ ለሚያፋጁን ምናቸውም አያደለም::

እኔ ጸሃፊዋ በእስራት በድብደባና ልገልጸው የሚያሳፍር ግፍ በወያኔ ተፈጽሞብኝ ችዬ መኖር ተስኖኝ ከምወዳቸው ሶስት ህጻናት ልጆቼ ነጥሎ ለስደት ያበቃን ለክፋትና ለተንኮል ወደር የማይገኝለትን የኢህአዴግ አገዛዝ በትግል ለመቀየር በተሟላ ስነልቦናዊ ብቃት እስከህይወት መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ ነኝ:: እንደ እኔ ያሉ የአገሬ ልጆች ቁጥራቸው ቀላል እንዳልሆነ ይሰማኛል::

በመሆኑም ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችና አባላት እውነት ተምራችሁና የዘመኑ ስልጣኔ ገብቷችሁ ከሆነ በአንድ አቅጣጫ በጽናት ቆማችሁ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ከበቂ በላይ ድብቅ ሃይል የበቃ አመራር አጥቶ ጊዘ በሰጠው ቅል ተፈረካክሰን እና ተበታትነን ከማለቃችን በፊት አትርፉን! በሚለው የህሊና ጥያቄ ጽሁፌን እደመድማለሁ::

ወያኔ ኢህአዴግ ይወድቃል
ግን ከእኔ በጽኑ መታገል ይጠበቃል!!

ተድላ ወሰኔ ነጋሽ - Tirschenreuth, Germany
ሚያዚያ 8 ቀን 2010 ጀርመን